# መናፍቁን ሙሴ

ደሃ እያራቆቱ ፣ በጉቦ ሙስና
እፍኝ ጥሬ ያጣ ፣ እዳው ግን በቁና
አይሰድቡ መሳደብ ፣ የከፋው ብልግና
ቀን ተሰየመለት ፣ ብለው ብልፅግና ።

ቀን አነሳን ብለው ፣ ሆነው ባለተራ
ሰላም እየነሱት ፣ ከኖረበት ስፍራ
ደሃ እያስለቀሱ ፣ ልባቸው አይራራ
ሰላም ቀን ይሉታል ፣ በጎሳ ምንጠራ
ይሳለቁበታል ፣ ዳርገው ለመከራ ።

አንጀቱ ተጣብቆ ፣ በቁም ሲያንቀላፋ
በርሃብ በጠኔ ፣ ሕዝብ እየተደፋ
በብድር በርጥባን ፣ ኑሮ እየተገፋ
በዝንተ ዓለም ውርደት ፣ አንገቱን የደፋ
የኩራት ቀን ብሎ ፣ ደሃውን ዘለፋ
ከዚህ የበለጠ ፣ ምን አለ የከፋ ።

ተግባር አልባ ትርክት ፣ ከንቱ በማቀንቀን
ስለጮኸ ብቻ ፣ ልክ እንደ በቀቀን
ስሙ ብቻ ያለ ፣ ተጥሎ የወደቀን
ቃላት አሳምሮ ፣ በምኞት መመርቀን
በግፍ እያሰሩ ፣ የዲሞክራሲ ቀን ።

በቋንቋ ልዩነት ፣ ሕዝብ እየበደሉ
ያለ ርህራሄ ፣ ሰው እየገደሉ
ደም እየተጋቱ ፣ አብጠው የወደሉ
ሰው አላግባብ አስሮ ፣ ፍርድ እያጓደሉ
የፍትሕ ቀን ብለው ፣ ይዘባበታሉ ።

ለፍቶ ያፈራውን ፣ ሰርቶ በጉልበቱ
እየተዘረፈ ፣ ሃብትና ንብረቱ
እያፈናቀሉ ፣ ዜጋውን ከቤቱ
እየዘመቱበት ፣ ዛሬም በሃይማኖቱ
ያንድነት ቀን ማለት ፣ የውዳሴ ከንቱ ።

መንፈሳዊ አይደለ ፣ የገዳም መነኩሴ
ፆም ፀሎትን አያውቅ ፣ ማህሌት ቅዳሴ
በታኙን ያንድነት ፣ አርገን እንደራሴ
ቸኩለን ምስጋና ፣ በከንቱ ውዳሴ
ያላግባብ ብንሰይም ፣ መናፍቁን ሙሴ
አምላክም ተጣላን ፣ አዘኑ ስላሴ ።

ታዛቢው

September 10, 2019